# ጣት ገማ ተብሎ .....

በተረትና ምሳሌና በቅኔ ከበለጸጉ አገሮች መካከል በዋንኛነት ልትጠራ የምትችል አገር ናት ኢትዮጵያ። ስለሁሉም ነገር ተረትና ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ነገር ግን ያለ አግባብ የምንጠቀምባቸው ወይም ትርጉማቸውን ከፉኛ የምንለጥጣቸውና ወደተሳሳተ ምሳሌነት የምንወስዳቸውም አሉና ለቅኔና ለተረትና ምሳሌዎች አጠቃቀም ቁጥጥር ሊያስፈልገን ነው። ለዛሬው ጽሁፌ ልንደረደርበት የምፈልገው ተረትና ምሳሌ ***"ጣት ገማ ተብሎ ተቆርጦ አይጣልም"*** የሚለውን ነው። ለምን አይቆረጥ አረ ተቀንጥሶ የሚጣልበትም ሁኔታ አለ ብላችሁስ?

እኔና ህክምና የምንተዋወቀው በችግር ቀን ብቻ ነው። ግን እንዲሁ በወሬ ወሬ ከምሰማው በመነሳት ጣት ላይ አደጋ ቢደርስ የቆሰሉና በትግል ሜዳ ያለቁ ነጭ የደም ሴሎችንና የተውሳኮችን ሽታ አጸዳድቶ 'ኢንፌክሽን' እንዳይበረታ በአልኮል ተጣጥቦ ለነጭ የደም ሴል እገዛ የሚሆን የአንቲ ባዮቲክ መሳርያ በመርፌ ተጭኖ በደም ስር በኩል ይላክና የመዳን ተስፋው ይጠበቃል። ነገር ግን በጣት ላይ ያለው ኢንፌክሽን ወደ እጅ ሊዘምት የሚችል ከሆነና እንዲያም እያለ ሕይወትም ጭምር ሊያጠፋ የሚችል 'ካንሰረስ' ከሆነ ለጉዳተኛው ጣት የስንብት ደብዳቤ በራሱ በባለ ጣቱ ተፈርሞለት ተቆርጦ እንዲጣል ይደረጋል። ስለዚህ ተረትና ምሳሌው የሚሰራው የጣቱ ግማት እስከ ሕይወት መጥፋት የማያደርስና የመዳን ተስፋ ያለው ከሆነ ብቻ ነው። ወንድምም እህትም ቢሆኑ በሌላው ሕልውና ላይ የሚያደቡና ተመክረው የማይመለሱ ከሆነ ከተረትና ምሳሌዎቹ አንዱ ይመዘዝና ብያኔ ይሰጣል "... ምከረው ምከረው እምቢ ሲል መከራ ይምከረው" ተብሎ።

አዎን በዚህ ቀውጢ ሰአት ተረትና ምሳሌው ላይ እደሳ ለማድረግ አይደለም መነሳቴ። ይልቁንም ይህን ተረት እየተጠቀሙ አገር አፍራሾችንና ወገን አጥፊዎችን ከጉያችን ለመሸጎጥ የሚደረገው ሙከራ ትክክል አይደለም ለማለት ነው። " ...... ወያኔዎችም ወንድሞቻችን ናቸው ጣት ገማ ተብሎ ተቆርጦ አይጣልም እንደሚባለው አናክርባቸው ..." የሚሉ እውቀትና እድሜ የጠገቡ ሰዎች እንዲሁም የኔ ቢጤ የዋሆች ተረትና ምሳሌውን ሲደጋግሙት ይሰማል። ነገር ግን እስከመቼ ድረስ? እኛንና ሀገራችንን ምን እስኪያደርጉ ድረስ ነው እንደማይጣለው የገማ ጣት የምናያቸው? የሚለው ጥያቄ ሊመረመር የሚገባውና ማሰርያ መቁዋጫም ሊገኝለት የሚገባው ጉዳይ ነው የሚል ማሳሰብያ ለመስጠት ነው።

ተረቱ ምናልባት ሊሰራ የሚችለው ወያኔዎች ተራ አምባ ገነን ቢሆኑ፣ ሌብነትና ዘረፋ ውስጥ ቢሰማሩ፣ ፍርድ ቢያጎድሉ ወይም ዘረኛ ብቻ ቢሆኑ ኖሮ አረ ተመከሩ፣ ይሄ ነገር አያዋጣም እየተባሉ አንዳንዴም ለመገሰጥ ሙከራ እያደረጉ መንገድ እንደሳቱ ልጆች ወደ ቀናው ልንመልሳቸው፣ ልናባብላቸው እንጂ ተስፋ ልንቆርጥባቸው አይገባም የሚሉንን እስቲ ይሁን ባልን ነበር። ነገር ግን ድርጊታቸው ከዚህ በጣም የከፋና እጅግ የጠለቀ ነው። ኢትዮጵያ እንደ አገር ሕዝብዋም እንድ አንድ አገር ሕዝብ እንዳይሆን ይተጋሉ። ድንበርዋን ያስደፍራሉ። አልፈው ተርፈው ለምለምና መሀል አገርን ለውጭ አገሮች እየቸበቸቡ ነው። የህዝብ ሀብትን የራሳቸው ሱቅ አድርገዋል፣ ባለሀብቶችን ወርሰዋል የአገር አስተዳደር አልባንያ አልባንያን መሸተት ከጀመረ ስንብቷል። ይህ ተራና በቀን ሂደት ሊለወጥ የሚችል ቀላል ነገር ነው የምንል ከሆነ የአደጋውን መጠን አልተረዳነውም ማለት ነው። ኢትዮጵያ እኮ ከዳር ወደ መሀል ከመሀልም ወደ ዳር እየፈረሰች ነው ያውም በፍጥነት። ይህን ተውሳክ በአልኮልና በአንቲ ባዮቲክ እንደሚፈወስ በሽታ መቁጠር የሬሳ ሳጥን ውስጥ ጋደም ብሎ ለገዳዩ ሚስማርና መዶሻ የማቀበልን ያህል ነው።

በትክክል የማስታውሰው ከሆነ ወንድሜ አብርሀ በኢትዮሚድያ አናት ላይ በእንግሊዝኛ "... ወያኔ (TPLF) ሊሻሻል የማይችል፣ ሊወገድ የሚገባው ድርጅት ነው ። ...." የሚል ጠንካራ መልእክት ለወራት አስነብቦን ነበር። ማሌሊት ለሀገራችን 'ካንሰረስ' የሆነ ድርጅት መሆኑን ዛሬ የማይቀበል ቢኖር ራሱ ወያኔና ሆድ አደር የሆኑ አውቀው የጨፈኑ ወገኖች ብቻ ናቸው። አውቀው የጨፈኑ ደግሞ ሞቱ ቢመጣም አሳምረህ ግደለኝ ይሉ እንደሆን እንጂ ፈውስ ፍለጋ አይተጉምና ካሉ ሊቆጠሩ አይገባም። ስለዚህ ጣት ገማ ተብሎ ተቆርጦ አይጣልም የሚለውን ተረትና ምሳሌ በአግባቡ እንጠቀምበት። ወያኔ የአረመኔነትን ሬከርድ የበጠሰ ለማንም ለምንም የማይመለስ የጥፋት መልእክተኛ ነው። በጎጥ በኩል የገባው ካንሰር በሀገር ፍቅር 'ኪሞ ቴራፒም' ከማይፈወስበት ደረጃ እንዳይደርስ የሚተጉ ሀይሎችን ማስወገድ ጊዜው አሁን ነው። ላለማጥፋት ያደረጉት አንዳች ነገር የለምና ካልበረታን ይበረቱብናል፣ ከፈቀድን ያጠፉናል ቀመሩ ይኸው ነው ምርጫውም በእጃችን ነው። የሚሻለን ግን መበርታት ብቻ ነው።

ደህና ሁኑልኝ

ዳኛቸው ቢያድግልኝ